# ዓይነ-ሞራችንን እንግለጥ

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*

በቱኒሲያ፣ በግብጽ፣ በቲቤትና በኢትዮጵያ እንደታየው ይህ ዘመን ሰዎች በክብር መገፈፍና በፍትህ እጦት ውስጥ ውስጡን እንደተዳፈነ ኩበት ከመንደድ አልፈው ከላይ ገላቸውን ቤንዚን እያርከፈከፉ የሚያቃጥሉበት ዘመን ሆኗል። [1-5] ይህም ብቻ አይደለም። ገሚሱ ግፍ እንዲያከትም ራሳቸውን መስዋእት ላደረጉት ጸሎት እያደረሰ፣ ድጋፉን እየገለጸና የሞቱለትን አላማ ከግብ ለማድረስ ቁርጠኝነቱን የሚያሳይበት፤ ሌላው ደግሞ እነዚህን የግፍ ሰለባዎች እብዶችና ወንጀለኞች እያለ የሚሳለቅበትና የሚዘልፍበት አስተዛዛቢ ወቅትም ሆኗል። ያሳዝናል!

የሥነ-ልቡና ባለሙያዎች የሚሰጡትን የእብደት ፍች ለጊዜው ትተን ህብረተሰብ በዘልማድ በእብድነት የሚፈርጃቸውን ባህሪዎች ብናጤን እንደ ህብረተሰቡ፣ እንደ ሰፈሩ፣ እንደ ቡድኑ አለዚያም እንደ ቤቱ የሚለያዩ ሆነው እናገኛቸዋለን። ካለገቦ ሥርዓቱን ተከትሎ የናይጀሪያ መንጃ ፈቃድ ለማውጣት በሞከረ አንድ የስራ ባልደረባዬ ላይ ሌሎች ቀርቶ መንጃ ፈቃዱን የሚሰጡት ባለስልጣናት ሳይቀር እንደ ቂል ወይም እብድ ቆጥረው ተክተክ ብለው እንደሳቁበት አጫውቶኛል። በተለያዩ መቅቡጦች ሊታለሉ ያልቻሉ አንድ የአገራችን ካህን እንደዚሁ ለገንዘብና ለስልጣን ሲሉ የአስራት ከፋዩን ምእመናን የመከራ-ዘመን ጩኸት ችላ ብለው ራሱን የቤተ-ክርስቲያን ተጠሪ አድርጎ የሚቆጥረውን ቡድን በማገልገል ላይ ባሉ በአንዳንድ የጊዜው ቀሳውስትና "ጳጳሳት" ዘንድ በኋላ-ቀርነት፣ በቂልነትና በእብድነት እንደሚታወቁ አውስተውኛል።

ስለዚህ ቅጥፈትና ክህደት ልጅ ወልደው በሚታረሱበት ቤት ውስጥ እውነተኛ ሰው እብድ ወይም ወንጀለኛ ነው። በተመሳሳይ መንገድ እውነትና ታማኝነት በነገሱበት ሰፈር ደግሞ ውሸታም ሰው እብድ ነው። እንግዲህ ለእውነትና ለፍትህ ሲል ገላውን አቃጥሎ ህይወቱን በምድር የተከለ ሰው ከነማን ቤት እንደ ሰማእት፤ ከነማን ሰፈር ደግሞ እንደ እብድ ወይም ወንጀለኛ እንደሚቆጠር ግልጽ ነው ማለት ነው።

ከአገራቸው ወይም ከአካባቢያቸው ማህበረሰብ አንድ ወይም ሁለት ስንዝር ላቅ ብለው የተገኙ ወይም ለእውነትና ለፍትህ የቆሙ ሰዎችን እንደ እብድ መቁጠር ዛሬ አልተጀመረም። ሶቅራጥስ ለእውነትና ለፍትህ ሲታገል የሚታገልለት ሕዝብ ሳይቀር እንደ እብድ ያየው ነበር። በኋላም ይኸው የሚሰቃይለት  ሕዝብ ድምጽ ሰጥቶ መርዝ ጨልጦ እንዲሞት አደረገው። [6-7] ከሞተ በኋላም ይኸው ሕዝብ ቃሉን ሽሮ መዳን እንኳን የማይችል ጂል ብሎ ዘለፈው። የድህነት ቡትቶ ኮታቸውን ደርበው በአውሮጳ ፍትህ እንዲሰፍን በተባ ብእራቸው ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረከቱት እንደ እስፓይኖዛና ቮልቴየር ያሉት ጠበብትም እንደ እብዶችና ወንጀለኞች እየተቆጠሩ ይታሰሩና ይሰደዱ ነበር። [6] አቡነ ጴጥሮስ ለፋሽሽት አልንበረከክም ብለው መሰዋታቸውን በምናደንቅበት አንድ ወቅት ለጠላት ለጊዜው እሽ ብለው ህይወታቸውን ማትረፍ የተሳናቸው ቂል አድርጎ የቆጠራቸው ዜጋ ገጥሞኛል። እንደ እብድ እየተቆጠሩ ሳይሰቃዩና ሳይሰደዱ ለዓለም መሻሻል ከፍተኛ አስተዋጾ ያበረከቱ ጠቢባን እንደዚሁም የፍትህና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ያሉ አይመስለኝም። የማታ ማታ ግን አለም ወደፊት የምትሽከረከረውና ሰው በሰውነቱ ተከብሮ የፍትህ አየርን እየተነፈሰ ተንቀባሮ ሊኖር የሚችለው በእነዚህ እብድ እየተባሉ ላባቸውንና ደማቸውን ማፍሰስ ብቻ ሳይሆን ህይወታቸውንም አሳልፈው በሰጡ የሰው ልጆች አማካኝነት ነው።

እንግዲህ እንደነዚህ አይነት ሰማእታት ለሰው ልጅ ክብርና ለፍትህ መስፈን ሲሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ህይወታቸውን አሳልፈው ሲሰጡ ሌሎች እነዚህን ብቁ ሰዎች ለምን በእብደት ወይም በወንጀል እየከሰሱ ቆመው እየሄዱ ስጋቸውን ይጠብሱታል? ሲሞቱስ ለምን ስማቸውን ያጎድፉታል? አንዳንዱስ እንኳን ቆሞ ለሚሄድ በሬሳ ሳጥን ውስጥ ለገባ ሰው እንኳ ለማይተኙት እንደነዚህ አይነት ግፈኞች ለምን ደጋፊና ተለላኪ ሆኖ ኑሮውን ይገፋል? እንደነዚህ አይነት ጥያቄዎችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለመመለስ ሰፋ ያለ ጥናት ማድረግ የሚያስፈልግ መሆኑ አጠያቂ አይደለም።  ቢሆንም እነዚህ ግፍኞችና ሎሌዎቻቸው በህብረተሰብ ውስጥ ከሚያሳዩት ገደብ የሌለው ስግብግብነት በመነሳት ብዙ ሰዎች ግፍኛ ወይም የግፈኛ ተባባሪ መሆንን እንደ ስልጣንና ገንዘብ ከመሳሰሉት ጥቅማጥቅሞች ጋር ያገናኙዋል። አንዳንዱም ከእርግማን ጋር ያዛምደዋል። እንደኔ እንደኔ ግን ከብዙ ምክንያቶች ውስጥ ዋናው የአይነ-ሞራ ጉዳይ ይመስለኛል።

ጥሬ ቃሉ እንደሚያመለክተው ዓይነ-ሞራ የዓይንን ብሌን የሚሸፍን በሽታ ወይም ደግሞ በህክምና ቃል ካታራክት የሚባለው ነው። ነገር ግን በአገራችን አባቶች አባባሉን የሚጠቀሙበት እውነት ወይም ጥበብ የተገለጠለትን ካልተገለጠለት ለመለየት ይመስለኛል። "ዓይነ-ሞራው ሲገለጥለት መልካሙ መንገድ ታዬው" እንዲሉ። በእርግጥ አይነ-ሞራ ከስልጣን የተደረተ ድሪቶ ወይም ከጨኻራ የለፋ ስልቻ ሊሆን ይችላል። ማን ያውቃል! አንዳንዶች እንደሚሉት ከምታት የወረደ መጋረጃ ሊሆንም ይችላል። ያም ሆነ ይህ እውነትንና ፍትህን ለማየት የሚያስፈልገው ከዲግሪ ወይም ከአሁኑ ዘመን ቆብ የተሰራ መነጽር ሳይሆን አይነ-ሞራን ሙልጭ አርጎ የሚገፍ "ሰውነትህን-ፈትሽ" የሚባል የቀዶ ጥገና ቢላዋ ነው።

የአረቡን ዓለም የለውጥ ማእበል ያጥለቀለቀው አብዛኛው ተንታኝ እንደሚለው በምጣኔ ሐብቱ መሽመድመድ ወይም ደግሞ በድሃው ቁጥር መናር አለዚም በአፈናው እየከፋ መሄድ ምክንያት አይመስለኝም። የድህነቱም ሆነ የጭቆናው መጠን ከዚህ የከፋባቸው ዘመኖች ነበሩ። የድህነት መስፋፋት ወይም የስራ-አጥ ቁጥር መናር በራሱ ሕዝብን ለለውጥ የሚቀሰቅስ በቂ ምክንያንት ቢሆን ኖሮ ከአውሬም የከፉት አምባገነኖች ችጋር ዋናው የሞት ምክንያት ከሆነባቸውን የሰሃራ በታች አገሮች ገና ድሮ ተጠራርገው በተወገዱ ነበር። ወዲያውም የሰው ክብር ተረገጠ ወይም ፍትህ ተጓደለ ብሎ ሳይሆን በመራቡ ወይም ስራ በማጣቱ ብቻ ያመጸ ሰው ሲመግቡት ጭድ በልቶ እንደጠገበ በሬ የበላውን እያገሳ በክብሩ ላይ እንደገና መተኛቱ የማይቀር ነው። እንደኔ እንደኔ ሕዝብ ለክብሩና ለፍትህ ራሱን አሳልፎ የሚሰጠው ሲርበውና ስራ ሲያጣ ሳይሆን ክብሩን ተገፎና ፍትህን ተነፍጎ ሲገዛ ከጋማ ከብት ያልተሻለ እንሰሳ መሆኑን ለማየት ዓይኑ-ሞራውን የገለጠ እለት ነው።

አዎ! ዓይኑ-ሞራው ሙልጭ ብሎ የተገለጠ ሙሉሰው ሰው መሆንን በራስ ናላ ከመገዛትና ከፍትህ  ነጥሎ ስለማያይ እንኳን የሌላውን ስብእና ሊገፍ እነዚህን የሰው መለያ ጸጋዎች ከሚነጠቅ የአካል ግዞትና ሞትን ይመርጣል። በሌላ አነጋገር ዓይኑ-ሞራው እንደ ተነፋ ጎማ ደንድኖ ያልጋረደው ከንቱ ለስልጣን ወይም ለገንዘብ ሲል የሌላ ሰው ነፍስ አያጠፋም ወይም አያሰቃይም። በዓይኑ-ሞራ ያልተሸፈነ ሰው ከነፍሰ-ገዳይ፣ ከዘረኛ ወይም ሌላ አይነት ኢሰብአዊ ፍጡር ጎንና ጀርባ አይቆምም። ዓይኑ-ሞራው ያላወረው ጉድ ዓይኑ-ሞራውን የገለጠ ሰው እብድ ብሎ አይጠራም፤ በወንጀለኝነትም አይፈርጅም። ዓይኑ-ሞራው ያልጋረደው ሰው ሌላው በግፈኞች ሲሰቃይና እንደ ሚዶቋ እየታደነ ሲገደል ያላዬ መስሎ ዝም አይልም። ዓይኑ-ሞራው ህሊናውን ያልከለለው ሰው "ነፍሴ ከመኖ ሌላ ምን ትፈልጋለች?" እያለ ራሱን ከመጠየቅ አይቆጠብም።

በአጠቃላይ ለሰው ልጅ ክብርና ለፍትህ መስፈን ሲሉ ህይወታቸውን በሚሰውትና በሌላው መካከል ያለው ልዩነት በድህነት የመጠፈርና ያለመጠፈር ሳይሆን የዓይኑ-ሞራ መገለጥና አለመገለጥ ጉዳይ ይመስለኛል። እንኳን በሃያ-አንደኛው ክፍለ-ዘመን በማንኛውም ጊዜም ቢሆን ሰው እንደ ለማዳ እንሰሳ አይንህ ሸፍን ሲሉት እየሸፈነ፣ጆሮህን ወትፍ ሲሉት እየወተፈ፣ አንደበትህን ዝጋ ሲሉት ጥርቅም እያደረገ፤ ጉርሻ ሲጥሉለት እየሰለቀጠ፣ ተጫን ሲሉት እየተጫነ፣ ታሰር ሲሉት እየታሰረ፣ ተኛ ሲሉት ለጥ እያለ፣ ተገረፍ ሲሉት እየተገረፈ፣ ሊገሉት ሲፈልጉም አንገቱን እየሰጠ መኖር የለበትም። ዓይኑ-ሞራችንን ከልሎን አልታዬን ብሎ እንጅ በመኖር ላይ ያለነው በዚህ መልኩ ይመስለኛል። ስለዚህ አምላክ ባርኮ ለሰጠን ሰብአዊ ክብራችን ሲሉ ህይወታቸውን እንደገበሩት ክቡራን በክብር ኖረን በክብር ለማለፍ፤ የሰው መልክ ይዘን እንደ እንሰሳ ከመኖር እንድንድን፤ እንደዚሁም ጸታ፣ቀለም፣ ቋንቋና ክልል-አልባ የሆነችው ፍትህ ፍንትው ብላ እንድትታየን ሰውነትህን-ፈትሽ በሚባለው ቢላዋ ዓይኑ-ሞራችንን እንግለጥ። አመሰግናለሁ።

**ዋቢ** (all last accessed on 11/20/2011)

1. Mohamed Bouazizi, http://en.wikipedia.org/wiki/Mohamed_Bouazizi
2. Egyptian man dies after setting himself alight, http://www.bbc.co.uk/news/world-middle-east-12214090
3. Eighth Tibetan burns himself in protest in China, Reuters   http://news.yahoo.com/eighth-tibetan-burns-himself-protest-china-051224439.html
4. Ethiopian Man Sets Himself On Fire In Protest Against Governmenthttp: African Spotlight http//africanspotlight.com/2011/11/ethiopian-man-sets-himself-on-fire-in-protest-against-government/
5. Ethiopian Activist Sets himself on fire, Abebe Gellaw http://addisvoice.com/2011/11/ethiopian-bouazizi-sets-himself-on-fire/
6. The story of Phylosphy, Will Durant, 1955 edition
7. Socrates, http://plato.stanford.edu/entries/socrates/

*ጥቅምት ሁለት ሺ አራት ዓ.ም.*